# የኢትዮጵያ ወደብ አልባነት እያስከተለ ያለው ጉዳትና ቀጣዩ አቅጣጫ

**ከጊዜው ደረሰ**

ሚያዝያ 2፣ 2008

(አፕሪል 10፣ 2016)

ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ በሀገራችን ህልውና ላይ ከፈጸሙት ስህተቶች ሁሉ ትልቁ የሀገራችንን ታሪካዊም ይሁን ህጋዊ መብት ወደጎን በመተው በግል ውሳኔያቸው ኤርትራን በተመለከተ በአቶ ኢሳያስ የሚመራው ቡድን የጠየቃቸውን ሁሉ ያለአንዳች ማመናታት መስጠታቸው ነበር። በአወሮፓውያን አቆጣጠር 1994 የፈጸሙትን ስህተት ደግሞ በ1998 ማረም የሚያስችላቸው ሁኔታ ቢፈጠርም ይህንን እድል ሳይጠቀሙበት ሆን ብለው ማለፋቸው ብቻ ሳይሆን እንዲያውም እድሉን እንጠቀምበት ያሉትን ሁሉ በተለያየ የሀሰት ክስ በመክሰስ ፣ ማሰራቸው፣ ከስራ ማባረራቸው፣ ማሰቃየታቸው ወዘተ በታላቅ ምሬትና ሀዘን የሚታወስ በሀገራችንም ታሪካ እንደ ትልቅ ጠባሳ የሚቆጠር የታሪክ አሻራ ነው። ይህ መሰረታዊ ስህተት በሀገራችን ላይ እያደረሰ የሚገኘው አደጋ እስከዛሬም በብዙ መልኩ ለእድገታችንም ሆነ ለመሰረታዊ ህልውናችን አደጋ ሆኖ ይገኛል።

በዚህ ጽሁፍ ይህ ስህተት ባሁኑ ስአት ከሚታየው ርሀብና በህዝባችን ላይ ከደረሰው አደጋ እንዲሁም ከመሰረታዊ የልማት ጉዞ አኳያ ያስከተለውን ተጽእኖ በመጠኑ አሳያለሁ።ይህንንም በማድረግ ከእርስ በእርስ ፍራቻ ተላቀን ፣ ካፈርኩ አይመልሰኝ የሚል ስሜትን አስወግደን እያነዳንዳችን የፖለቲካ ልዩ ጠቀሜታ ሳይሆን ሀገርንና ህዝብን ለመታደግ ምን መደረግ እንዳለበት ለመነጋገር ተጨማሪ መንደርደሪያ ይሆናል ብየ አስባለሁ። የጉዳቱ ስፋት ከኢኮኖሚና እድገት አኳያ ሲታይ ኢትዮጵያ ከምተገኝበት እጅግ ወደ ሓላ የቀረ ሁኔታ ለመላቀቅ እጅግ ብዙ ገንዘብ ያሰፈልጋታል። ይህን ለማድረግ ደግሞ ወይ ገቢዋን እጅግ ማሳደግ ይኖርባታል ወይም ደግሞ ወጪዋን መቀነስ ይሆርባታት። ከገቢ ወጭ የሚተርፍ ገንዘብ ነው አንድን ሀገር ሀብት እንድታከማች ወይም አዳዲስ የልማት ስራወችን ለመሰራት አቅም እንዲኖራት ወይም ለክፉ ጊዜ የሚሆን መጠባበቂያ እንዲኖራት የሚያደርገው፡፡

በሀገራችን አሁን እየተካሄደ ነው እየተባለ የሚነገረን የልማት ስራ ባብዛኛው የሚካሄደው ወይ በእርዳታ ወይም በብድር በሚገኝ ገንዘብ ነው ። ይህ የራሱ ችግር አለው። ብድር ጊዜውን ጠብቆ ከነወለዱ መከፈል ይኖርበታል።ይህ ሲሆን ደግሞ ያለ የሌለን ሀብት አሟጦ ለአበዳሪው ነው የሚያስረክበው። ባብዛኛው የሶስተኛው አለም ሀገሮች፣ የተበደሩት ገንዘብና ወለዱ ለመክፈል ከሚችሉት አቅም በላይ እየሆነ ከማይወጡበት ማጥ ውስጥ እንደሚወድቁ የሚታወቅ ነው፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያም የዚሁ ሁኔታ ሰለባ ነበረች፡፡ ኢትዮጵያ የብድሯ መጠን ለመክፈል ከምትችለው በላይ እንደሆነ ታውቆ ከአመታት በፊት የብድር ምህረት (ብድር ስረዛ) ተደርጎላት ነበር። አሁን ደግሞ ኢትዮጵያ የምትበደረው ገንዘብ ከአመት አመት በፈጣን ሁኔታ እያደገ ነው፡ በዚህ ከቀጠለም ለመጭው ትውልድ የምታስተላልፈው እዳ እንጂ ሀብትን አይሆንም። የሀገራችንን ያለ የሌለ ሀብት በከፍተኛ ደረጃ በማራቆት ላይ የሚገኘው አንዱ ወደውጭ ለሚላከውና ወደሀገር ለሚገባው ሸቀጥና ምርት የምትከፍለው የወደብ ኪራይና ቀረጥ ወጭ ነው። ይህ ወጭ ከአመት አመት እየጨመረና ከአቅም በላይ እየሆነ በመሄድ ላይ ነው። ይሀ ሁሉ እዳ የመጣብን ደግሞ ባለሁለት ወደብ የነበረችው ሀገራችን ወደብ አልባ በመሆኗ ነው።

በዚህ አንጻር ለኢሳያስ ( ሸአብያ) አገዛዝ አሳልፎ የተሰጠው የኢትዮጵያ ታሪካዊና ህጋዊ ግዛት በመሰረታዊ እድገታችንና አቅም ግንባታ ላይ እያደረገ ያለውን ቀጥተኛ ተጽእኖ በመጠኑም ቢሆን መመልከት ይጠቅማል። ሸአብያ ኤርትራን ተረክቦ አስመራ

ላይ መንግስት ከመሰረተ ወዲህ ኢትዮጵያ በአሰብም ሆነ በምጽዋ ወደቦች በኩል ለምታስገባውም ሆነ ወደውጭ ለምትልከው ምርት (እቃ) ለአቶ ኢሳያስ መንግስት ቀረጥ እና፣ የወደብ ኪራይ ስትከፍል ቆይታለች፡፤ በአውሮፓ አቆጣጠር ከ 1998 ጦርነት ወዲህ ደግሞ የአሰብንም ሆነ የምጽዋን ወደብ መጠቀም አቁማ የወጭና የገቢ ንግዷን በጂቡቲ በኩል ካደረገች በሓላ ለጅቡቲ የምትከፍለው ገንዘብ እጅግ ብዙ ሆኗል፡፡

ይህ ወጪ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ በመሄድ ላይ ነው። በአሁኑ ሰአት የኢትዮጵያ የገቢና ወጪ ንግድ ዘጠና ከመቶ (90%) ያክሉ የሚካሄደው በጂቡቲ በኩል ፡ ነው። የኢትዮጵያ የፋይናነስና የኢኮኖሚ እድገት ሚኒስቴር የነበሩት አቶ አህመድ ሽዴ በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ 2012 ላይ እንደተናገሩት " ኢትዮጵያ ለባህር ወደብ ክፍያ በየእለቱ ሁለት ሚሊየን የአሜሪካ ዶላር ትከፍላለች"፡፡

ይህም ማለት የሀገሪቱን የውጭ ንግድ 16% ያክሉን ለጅቡቲ የወደብ ኪራይ ታሰረክባለች ማለት ነው። http://addisstandard.com/ethiopia-spending-two-million-usd-per-day-for-transit-costs/ የአለም ባንክ የ 2013 ሪፖርት እንደሚያሳየው የራሳቸው ወደብ የሌላቸው ሀገሮች አንድ ኮንቴነር እቃን ወደውጭ ለመላክ የሚያወጡት ውጪ ባውሮፓውያን አቆጣጠር በ 2006 አሜሪካን ዶላር 2220 ነበር። ይህ ዋጋ በ 2013 አመት ምህረት ወደ 3000 ያሜሪካን ዶላር ከፍ ብሏል። ባንጻሩ የራሳቸው ወደብ ያላቸው ሀገሮች ለተመሳሳይ ኮንቴይነር ወጫቸው በግማሽ (50%) ዝቅ ይላል። http://addisstandard.com/ethiopia-spending-two-million-usd-per-day-for-transit-costs/ ይህን ሁኔታ ከሀገራችን እውነታ ጋር ስናዛምደው እጅግ የሚዘገንን ሁኔታን እናያለን፡፡ራሱ መንግስት ያመነው ለጅቡቲ የሚከፈለው በቀን 2 ሚሊዮን ዶላር የወደብ ወጪ የራሳችን ወደብ ቢኖረን ወጭው በ 50% ይቀንስ ነበር ብለን ብናስብ እንኳ የራሳችን ወገን የሆነውን የአፋር ህዝብ መኖሪያ የሆነውን የአሰብን ወደብ መጠቀም ባለመቻላችን የምንከፍለው እዳ በቀን በቀን 1 (አንድ) ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር ማለትም ባሁኑ ምንዛሬ ስሌት (በ 21 የ ኢትዮጵያ ብር ምንዛሬ በቀን 21 ሚሊየን ብር ) በአመት ደግሞ 365 ሚሊዮን ዶላር ማለትም 7፣ ቢሊዮን፣ 665፣ ሽህ የኢትዮጵያ ብር ያክል ኢትዮጵያ ታጣለች ማለት ነው ።

ይህ በዝቅተኛ ስሌት ሲታሰብ ነው። በዚህ ስሌት ላለፉት 15 አመታት ብቻ የደረሰውን አላስፈላጊ ወጭ ለማስላት (የባከነ ገንዘባችን) የዶላሩ ምንዛሬ በየጊዜው ስለሚለዋወጥ በማከላዊ ደረጃ ምንዛሬው 1 ዶላር በ 17 የኢትዮጵያ ብር ነበር ብለን ብንወስድ በ 15 አመት ውስጥ ያጣነው 15 X 365 = 5,475,000. (አምስት ቢሊየን አራት መቶ ስባ አምስት ሚሊየን የአሜሪካን ዶላር) በማከላዊ ምንዛሬ ባንድ ዶላር 17 የኢትዮጵያ ብር ሂሳብ ሲመነዘርም 93፣ ቢሊየን 075 ሽህ (ዘጠና ሶስት ቢሊየን ሰባ አምስት ሚሊየን) የኢትዮጵያ ብር ያክል ነው። የገንዘቡን መጠን በማየት ብቻ ሰርአቱ የወሰደው አርቆ አሳቢነት የጎደለው እርምጃ ምን ያህል ኪሳራ በሀገራችን ላይ እንዳደረሰ መረዳት የሚቻል ቢሆንም በዚህ ገንዘብ በሀገራችን ውስጥ ምን ማድረግ ይችላል (ይችል ነበር) የሚለውን መመልከት ደግሞ የሁኔታውን ተጽእኖ ይበልጥ ለመረዳት እንድንችል ይረዳናል።

የኢትዮጵያ ህዝብ እየከፈለ የሚገኘው ቀጣይ ዋጋ በአለፉት 15 አመታት የተከሰተውን ድርቅ ሙሉ በሙሉ ያለምንም የውጭ እርዳታ መቋቋምና አንድም ህጻን በረሀብ እንዳይሞት ማድረግ ይቻል ነበር ሀገራችን ባለፉት 15 አመታት ውስጥ ተከታታይ ድርቅና ረሀብን አሳልፋለች። በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ሁሉ ችግሩን ለመወጣት የሚሰፈልገው ገንዘብ የሚመጣው በማያቋርጥ ልመና ባብዛኛው ከባእዳን በተለይም ከምእራቡ መንግስታት ነው። ብዙዎች የዝናብ እጥረትና ድርቅ የተፈጥሮ ውጤት ስለሆኑ ከቁጥጥር ውጭ ናቸው ማንም ሊወቀስበት አይገባም ይላሉ፡ ይህ ትክክል አይደለም፣ ድርቅ ተፈጥሮአዊ ነው ብንል እንኳ፣ ይህ አይነቱ የተፈጥሮ መለዋወጥ የሚያስከትለውን አደጋ ለመቋቋም ሀገሪቱ ለምን በቂ መጠባበቂያ አላከማቸችም ወደሚለው ጥያቄ ይወስደናል። የተለያየ መረጃ በግልጽ እንደሚያሳየው፣ ሀገራችን ወድብ አልባ እንድትሆን በመደረጉ የተነሳ የምንከፍልውን ወጭ ማስወገድ ብንችል በየጊዜው የተከሰተውን ረሀብ ያላንዳች የውጭ እርዳታ ለመቋቋም የሚያስችል ሀብት ማከማቸት ትችላለች ።

ይህን በመረጃ ለመመልከት ያክል በምእራባውያን አቆጣጠር በ 2008 የተከሰተው 10 ሚሊየን ወገኖቻችንን ያጠቃውን ድርቅ ለመቋቋም ሀገራችን ያሰፈልጋታል ተብሎ የነበረው US$460 ዶላር ነበር http://www.wfp.org/content/ethiopia-caught-

middle-horn-africa-emergency ይህ ገንዘብ ባንድ አመት ከሶስት ወር ውስጥ ለጅቡቲ ለወደብ የምንከፍለው ገንዘብ ነው። አሁን በ 2015 /2016 ከአልኒኖ (El Niño) ጋር በተዛመደ የተከሰተው ድርቅ እስከ 15 ሚሊዮን የሚጠጉ ወገኖቻችንን በረሀብ እየገረፈ ይገኛል። ይህን አደጋ ለመቋቋም በሚቀጥሉት ስድስት ወራት $285 ሚሊየን ዶላር (£173m) ያሰፈልጋል ሲል የተባበሩት መንግስታት የምግብ ፕሮግራም ገልጧል http://news.bbc.co.uk/2/hi/africa/8319741.stm ። ምናልባትም በአመት ውስጥ ከላይ የተገለጸው ገንዘብ ሁለት እጥፍ ያስፈልጋል ብለን ብንገምት ባጠቃላይ እስከ 855 ሚሊየን ያሜሪካ ዶላር ያሰፈልጋል ማለት ነው።

ዲሰምበር 9፣ 2015 ታትሞ ለንባብ የበቃው ሪፖርተር ጋዜጣ ሀገሪቱን ባለስልጣናት ጠቅሶ አሁን የሚታየው ድርቅ እያስከተለ ያለውን ጉዳት ለመቋቋም 1.4 ቢሊየን ዶላር እንደሚያሰፈልግ ዘግቧል። ኢትዮጵያ በያመቱ 365 ሚሊዮን ዶላድ ያላግባብ ለጅቡቲ ለወደብ ክፍያ እንደምታወጣ ስናስብ ይህን ታይቶ የማይታወቅ እየተባለ የሚነገረውን ድርቅ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ ያለምንም የውጭ እርዳታ የአራት አመት የወደብ ወጫችን ብቻ ሊሸፍንልን እንደሚችል ማሰብ ተገቢ ነው። ይህ ባለመሆኑ ብዙ ሽህ ኢትዮጰያዊ ህጻናት ፣ አዛውንቶችና ሌሎችም ወገኖቻችን ምግብ አጥተው ህይወታቸው እየተቀጠፈ እንደሆነ ስንመለከት ከፍተኛ ብስጭትና፣መጠን የሌለው ቁጣ ቢሰማን ያለምክንያት አይደለም።

ለያንዳንዱ የሀገሪቱ ክልል 10 ቢሊየን 350 ሚሊየን (አስር ቢሊዮን 350 ሚሊየን) የኢትዮጵያ ብር ተጨማሪ በጀት መመደብ ይቻል ነበር። ኢትዮጵያ ባሁኑ ሰአት በ 9 ያስተዳደር ክልሎች የተዋቀረች ነች ፡ ይህ የባከነ ገንዘብ ለአያንዳንዱ ክልል እኩል ቢከፋፈልኖሮ አሁን ባላቸው አመታዊ በጀት ላይ በአመት በአመት ለያንዳንዱ ክልል ቢያንስ 690 ሽህ ( ስድስት መቶ ዘጠና ሽህ ብር ) በ 15 አመት ውስጥ ደግሞ ለያንዳንዱ ክልል 10 ቢሊየን 350 ሚሊየን የኢትዮጵያ ብር ተጨማሪ በጀት መመደብ ይቻል ነበር።ይህ ሲሆን ደግሞ በተጨማሪው ገንዘብ ምን ያክል መምህራንን፣ የጤና ባለሙያወችን ፣ የልማት ሰራተኞችን የእርሻ ባለሙያወችን መቅጠር እንደሚቻል ምን ያክል የልማት ሰራ መስራት እንደሚችል፣ ምን ያክል በየጎዳናው የሚንከራተቱ ህጻናትን፣ እናቶችና አዛውንቶችን ለመታደግ እንደሚያስችል ምን ያክል የድንገተኛ አደጋ መቋቋሚያ ፕሮጋራም ማዘጋጀት እንደሚቻል ወዘተ ማገናዘብ አስቸጋሪ አይደለም።

የዘንድሮውን የ 2008 (የ 2015/2016 ቱን) የሀገሪቱን አጠቃላይ በጀት 50% መሸፈን ይቻል ነበር ከሀሪቱ አጠቃላይ በጀት አኳያ ሲታይ ደግሞ፤ የኢያትዮጵያ ትልቁ ባጀት እየተባለ የሚጠቀሰው ባውሮፓውያን አቆጣጠር በ 2015 የተመደበው 11 ቢሊየን ዶላር ነው http://www.theeastafrican.co.ke/news/Ethiopia-presents--11-billion-budget/-/2558/2746828/-/olsdv9z/-/index.html ። ይህ ማለት ለ 15 አመት በወደብ አልባነታችን የባከነው ገንዘባችን የአገሪቱን ትልቁን በጀት ከ 50% በላይ ሊሸፍን በቻለ ነበር ማለት ነው። የሀገሪቱን ከፍተኛ የካፒታል በጀት ሙሉ በሙሉ መሸፈን ይቻል ነበር እንደ ሀገሪቱ የዘመኑ ባለስልጣኖች አነጋገር ከሆነ ለ 2015 (ባውሮፓውያን አቆጣጠር ) ከተመደበው በጀት ውስጥ ለአጠቃላይ ካፒታል ወጭ የተመደበው ገንዘብ ውስጥ 12.1 ቢሊየን ብር ከውጭ በብርድና በእርዳታ የሚገኝ ነው። ለጅቡቲ በ 2014 እና በ 2015 የተከፈለው የወደብ ክፍያ ብቻ ወደ ኢትዮጵያ ብር ሲመነዘር 365፣000x2x21 (አሁን ባለው ምንዛሬ መሰረት ) 15 ቢሊየን 330 ሽህ ብር ነው

ማለትም ያለምንም እዳና የውጭ እርዳታ የሁለቱ አመት በወደብ ክፍያ የምንፈልገውን የካቲታል ወጭ ሙሉ በሙሉ ሸፍኖ ከሶስት ቢሊየን ብር በላይ ለሌላ ጉዳይ ሊውል የሚችል ትርፍ ገንዘብ ማሰቀመጥ እንችል ነበር ማለት ነው። http://allafrica.com/stories/201406100219.html በዚህ ገንዘብም ምን ያክል እወራ ጎዳና፣ ሆስፒታሎች፣ ትምርት ቤቶች ጤና ጣቢያወች፣ የልማትና ምርምር ጣቢያወች፣ ፋብሪካወች ወዘተ መመስረት እንደሚቻል መገናዘብ አይከብድም በመላው ሀገሪቱ የአእምሮ ጤና አገልግሎትን ሙሉ በሙሉ ማዳረስ ይቻል ነበር ይህ በያመቱ በራሳችን ላይ ያመጣነው ኪሳራ በጤናና በትምህርት ያስከተለውን ተጽእኖ ለማመዛዘን ደግሞ በከፊል የሚከተለውን እንመልከት። ሐገራችን በአእምሮ ጤና አገልግሎት በኩል እጅግ ሐላ ቀር ከሚባሉት የአለም ክፍሎች የምትመደብ ነች። በዚህ ሙያ የሰለጠኑ የአእምሮ ጤንነት የህክምና ሌሎችም ባለሙያወች

(ሳይካትሪስቶች) ከሙቶ የማይበልጡ ናቸው፤ በመላ ሀገሪቱ ለዚህ አገልግሎት የተከፈቱ ሆስቲታሎች ከአራትና አምስት አይበልጡም። በአጠቃላይ የአምሮ ጤንነት ችግር የሚደርስባቸው ኢትዮጵያውአን ሁሉ እጅግ አሰቃቂ የሆነ ችግር ውስጥ ነው የሚገኙት። በቅርብ የወጣ አንድ ሰፋ ያለ ጥናት እንደሚያሳየው፣ ለዚህ ችግር መሰረታዊ አገልግሎት ለማቅረብ የሚፈለገው በጀት ለአምስት አመት የሚከተለውን ይመስላል፡ 20012/13 6,728,809.00 2013/14 7,389,362.00 2014/15 8,486,902.00 2015/16 9,866,846.50 ጠቅላላ 32,471,919.00http://www.centreforglobalmentalhealth.org/sites/www.centreforglobalmentalhealth.org/files/uploads/documents/ETHIOP~2.pdf ከላይ የተመለከተውን ወጭ በያንዳንዱ አመት ወጭ የሆነው የወደብ ክፍያ ገንዘብ ሙሉ በሙሉ በመሸፈን የተሟላ የአእምሮ ጤንንት እንክብካቤ በሚፈለገው ደረጃ በመላ ሀገሪቱ ለተጎዱ ወገኖቻችን ማድረስ ይቻል ነበር።

ይህ ደግሞ ተጎጂወችን ብቻ ሳይሆን ምን ያክል ቤተሰቦቻቸውንም እንደሚታደግ መገመቱ ከባድ አይደለም። በተሳሳተ የፖሊሲ ውሳኔ እና አሁንም በዚያው የተሳሳተ ፖሊሲ ውስጥ ስለተቀጠለ እነሆ ሀገራችን መሰረታዊ ህክምናን ለህዝቧ ማቅረብ አቅቷት ልመና ቀጥላለች። የአባይን ግድብ ግንባታ ያለምንም ብድርና የህዝብ መዋጮ መሸፈን ይቻል ነበር በአባይ ወንዝ ላይ የሚከናወነው ግድብ በአጠቃላይ ያሰፈልገዋል የሚባለው ወጭ 4 ቢሊየን ዶላር ነው። በወደብ አልባነታችን ምክንያት ላለፉት 15 አመታት ከባከነው ሀብታችን አንጻር ሰናየው (5,475,000) የባከነው ገንዘባችን የአባይን ግንባታ ሙሉ በሙሉ በራሳችን ወጭ ሸፍኖ 1.5 ቢሊየን ዶላር በላይ ለሌሎች ልማቶች ሊውል የሚችል ትርፍ ገንዘብ ሊኖረን በቻለ ነበር። ባጭሩ ከላይ የቀረበው የተወሰነ መረጃ እንደሚያሳየው ፣ የኤርትራን ከኢትዮጵያ መገንጠል በተመለከተ የኢትዮጲያን ጥቅምም ይሁን ታሪካዊና ህጋዊ መብት ለማስከበር እርምጃ ባለመወሰዱ እነሆ እድገታችንን እጅግ ጎድቶታል። ይህችን ኩሩ ታላቅ ሀገር የሌሎች ቋሚ ጥገኛ አድርጓታል።

ሁኔታው ካልተቀየረም ይህ ጉዳት እየባሰ እንጂ እየቀነሰ አይመጣም። የደህንንት ጉዳይስ ኢትዮጵያ የደረሰባትን ረሀብ ለመቋቋም ላለፉት ጥቂት ወራት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ እርዳታን ገንዘብ እየከፈለች በጅቡቲ በኩል እንደልብ ለማስገባት የገጠማትን ተግዳሮት ስንመለከት አያድረስ እንጅ ከጅቡቲ ጋር ጸብ ውስጥ ብንገባ ምን አህል አደጋ እንደተጋረጠንን ለመረዳት እጅግ አርቆ ማሰብን አይጠይቅም። በርግጥም ሀገራችን ወደብ አልባ በመሆኗ እስረኛ መሆኗን ሁሉም እያየው ነው።

ገዝወቻችን ያስተላለፉት ሀላፊነት የጎደለው ውሳኔ እነሆ አንድ ጊዜ በርበራ፣ ሌላ ጊዜ ሞምባሳና ፖርትሱዳን እንዲሯሯጡና ደጅ እንዲጠኑ እያደረጋቸው ይገኛል። በቀጣይነት ከመጎዳት ለመታደግ ምን ይደረግ? ከላይ እንደተመለከተው የሀገራችን ወደብ አልባ መሆን እያስከተለ ያለው ጉዳትና አደጋ ኢትዮጵያን እንወዳለን የወደፊት እድገቷንም እንመኛለን ለምንል ሁሉ እጅግ ሊያሳሰበን ይገባል። ሁኔታው አስቸኳይ መፍትሄን የሚሻ የልማት፣ የብሄራዊ ደህንነት እና የህልውና ጥያቄ ነው። ይህ ሁኔታ ከውይይታችን ሊርቅ ፈጽሞ የማይገባ ችላ የማይባል ሀገራዊ ጥያቄ ነው።

አወ ይህን ሁኔታ እንዲመጣ ያደረገው በስልጣን ላይ ያለው መንግስት በተለይም ደግሞ አቶ መለሰ ዜናዊ በግሉ የወሰዳቸው ሀላፊነት የጎደለው ተከታታይ እርምጃወች ናቸው። ያም ሆኖ ግን ማንም ያምጣው ማንም ዛሬ የሁላችንም እዳ ሆኗል። ስለዚህም መፍትሄ መፈለጉ የሁላችንም ጉዳይ ነው። አሁን በሚታየው ሁኔታ እየደማች ኢትዮጵያ ልትቀጥል ከቶውንም አይገባም፤አትችልምም።

ሁላችንም ኢትዮጵያውያን በተለያዩ ጉዳዮች ላይ የየራሳችን የፖለቲካ አመለካከት ቢኖረውም ይህን ቀጣይ አደጋ ማሰቆም እንደሚገባን ግን ማሰብ ይኖርብናል።ብሄራዊ ጥቅምን ለማስጠበቅ ከጠባብ ከፖለቲካ አመለካከትና ከግትር የአይዲዮሎጂ እስረኛነት በሻገር መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡የሀገራችን ወደብ አልባነት እያስከተለ ያለው ችግር ዛሬ የሁላችንም ችግር ነው ፤ መፍትሄውም በሁላችንም እጅ የሚገኝ ነው።

በኔ አስተሳሰብ አሁን ያለው ሁኔታ (statuesque ) በምንም መልኩ መቀጠል የለበትም፣ ይህ ከሆነ ኢትዮጵያ ምንም አይነት ቅን አሳቢወች ስልጣኑን ቢይዙ ወደሚፈለገው እድገት ሊያደርሷት አይችሉም፡፡ እንዲያውም እያደረ እና እየቆየ ሲሄድ መግቢያና መውጫችንን የተቆጣጠሩት አገሮች በህልውናችን ላይ እጅግ ትልቅ አደጋን ማድረሳቸው አይቀሬ ነው። ባጭሩ ሀገራችን

ሁል ጊዜ ህልውናዋና ደህንነቷ በራሷ እጅ ሳይሆን የባህር በሩን በተቆጣጠሩት ጎረቤቶቿ የሚወሰን ነው የሚሆነው ማለት ነው። ጎረቤቶቻችን ደግሞ እነማን እንደሆኑና ስለኢትዮጵያ ያላቸው ስሜትም ባብዛኛው ቅን እንዳልሆነ የሚታወቅ ነው። እያንዳንዱ ትውልድ ለመጭው ትውልድ ከወረሰው የተሻለ ሀገርን ማስተላለፍ ይገባዋል።

ይህ የአሁኑ ትውልድም ለቀጣዩ ትውልድ የሚያወርሰው ህልውናዋ አደጋ ላይ የተንጠለጠለ፣ በእዳ የተዘፈቀችና ለማያቋርጥ የኢኮኖሚና ብሄራዊ ደህንነት ችግር የተጋለጠች ሀገር መሆን የለበትም፡፡ ይህን ለማድረግም ከሁሉም በፊት ከተሳሳተው ፖሊሲ መላቀቅን እና የሀገራችንን ዘላቂ ጥቅም ታሪካዊና ህጋዊ መብት ለማስከበር በጋራ መቆም ይጠይቃል።

ታላላቅ መሪወች አሉላ አባ ነጋ፣ ቢትወደድ አሊ ሚራህ፣አጼ ዮሀንስ፤አጼ ሚኒሊክ፤ ታላቁ ጀነራል ጃጋማ ኬሎ ፊታውራሪ ዲነግዴና ሌሎቹም የኢትዮጵያን ታሪካዊና ህጋዊ ሀገራዊ መብት በተመለከተ የተናገሩትን ሁሉ ደግሞ ደጋግሞ ማሰብ መጭውም ትውልድ እንዲያውቀው ማድረግ አስፈላጊ ነው። ዛሬ ባይሆን ነገና ከነገ ወዲያ የኢትዮጵያ ህጋዊና ታሪካዊ መብቷ እንዲከበር ማድረግ የሁላችንም ሀላፊነት ነው። ይህ ታሪካዊና ህጋዊ መብት ተግባራዊ ሳይሆን የህዝብን ቀጣይ እድገትም ይሁን የአካባቢውን ሰላም ማረጋገጥ የሚቻል አይሆንም።

አምባሳደር ሄርማን ኮሀን የሚሰነዝሩት "አስብን ኢትዮጵያ በኪራይ እንድትጠቀም ለማድረግ ላደራድራችሁ " የሚለው እቅድ ህዝባችንን ለሀገሩና ለክብሩ ምን ያክል ቀናኢ እንደሆነ አለመረዳትና ለህዝባችንም ያላቸውን ዝቅ ያለ አመለካከት ያመለክታል። ለራሳችን ንብረት ኪራይ መክፈል አሳፋሪ ነው። መደረግ ያለበት ባለቤትነታችንን ማረጋገጥ ነው። የፈለገው ቢሆን ከኛ አናሳ የሆኑ እኛን በቀጣይነት እስረኛ እንዲያደርጉን መፍቀድ የለብንም። እነዚህን ታሪካዊ ስህተቶችን ለማረምና ሀገራዊ ተልእኮወችን እውን ለማድረግ ግን በመጀመሪያ የህዝባችንን አንድነት የሚያረጋግጥ በህዝባችን መካከል እርቅን የሚያሰፍን ተጨባጭ እርምጃን መውሰድ ይገባል።

ከጊዜው ደረሰ
( gezew.derese@bell.net )

http://www.ethiopanorama.com